| | |
|---|---|
| ዐይነት ⁝ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ⁝ | "በሀገር ፡ ድርድር ፡ የለም !" |
| ደራሲ ⁝ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ⁝ | ነሐሴ ፡ 2016 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ⁝ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ⁝ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2016-005 |
| ማስታወሻ ⁝ | |
| ማሳሰቢያ ⁝ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | افْتِتاحي

# በሀገር ፡ ድርድር ፡ የለም!



ላለፉት ፡ 100 ፡ ዓመታት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሲፈታተን ፡ የኖረው ፡ የምልክዮሽ ፡ ኀይል ፥ ገድሎ ፡ የሚነጥቅ ፡ እንጂ ፥ ተደራድሮ ፡ የሚስማማ ፡ አይደለም ። ድርድርን ፡ የሚፈልጋት ፡ አዘናግቶ ፡ ለመግደል ፥ የተመኘውንም ፡ ለመግፈፍ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በታሪክ ፡ ተደጋግሞ ፡ ታይቷል ።

ደጋግመን ፡ ብለነዋል ፥ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የምልክዮሽን ፡ የጥፋት ፡ ተልእኮ ፡ የሚፈጽም ፥ በራሱ ፡ በድን ፡ የኾነ ፡ እጅ ፡ እና ፡ እግር ፥ ራሱ ፡ ግን ፡ ባዕድ ፡ የኾነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠላት ፡ ነው ። ከበድን ፡ ጋራ ፡ መደራደር ፥ መደራደር ፡ አይበለው ፥ መሞኘት ፡ እንጂ! ራሱ ፡ ባዕድ ፡ ነው ፡ ብለናል ፥ አይገኝልንም! የሚገኙልን ፡ ጦርነት ፡ ያወጁብን ፡ እና ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ የሚገድሉን ፡ እጆቹ ፡ እና ፡ እግሮቹ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ እነርሱን ፡ ቈርጦ ፡ መጣል ፡ እንጂ ፡ ከበድኖች ፡ ጋራ ፡ መደራደር ፡ አይቻልም!

ጥቂት ፡ የፋኖ ፡ መሪ-ተብዬዎች ፡ የመደራደር ፡ ፍላጎት ፡ ያላቸው ፡ መኾናቸውን ፡ በምልክት ፡ አሳይተዋል ። ጠላት ፡ ድርድርን ፡ የፈለገበት ፡ ምክንያት ፥

- አንድም ፥ "ድርድሩ ፡ ከሸፈ!" ፡ ተብሎ ፡ በሕገ ፡ ውንብድናው ፡ አንቀጽ ፡ 39 ፡ መሠረት ፡ "ክልሎች ፡ የራሳቸውን ፡ ዕድል ፡ በራሳቸው ፡ ይወስኑ!" ፡ ተብሎ ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደ ፡ ሶቪየት ፡ ኅብረት ፡ ለመበታተን ፤
- አንድም ፥ በእንዝልዛይ ፡ ድርድር ፡ ጊዜ ፡ ለማግኘት ፡ እና ፥ በተረጋገጠ ፡ ኹኔታ ፡ ሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለማጥፋት ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሚታገለው ፥ ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ ለማስከበር ፡ እና ፡ ባዲስ ፡ ክዋኔ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥቱን ፡ ለመመሥረት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ የሕዝብ ፡ ክንድ ፡ የኾነው ፡ ፋኖ ፥ በጠላት ፡ የድርድር ፡ ዐቅድ ፡ ልምራኽ ፡ የሚለውን ፡ ግብዝ ፡ መሪ ፡ ኹሉ ፥ ጊዜ ፡ ሳይሰጥ ፡ ያስወግደዋል ❖

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2016 ፡ ዓ.ም. ።